# ሐሸማል



ማዕበል ፈጠነ

# ለሽማል

ዘማዐበል ፈጠነ

## መግለጫ

ንደማይቆጠሩት የሰማይ ከዋክብት የማይሰፈር ጥበብ በአባቶቻችን
ልብ ግድግዳ ተስትኋል። ከትውልዱ ርቆ የተሰቀለውን ጥበብ ቁመተ
ርጋዳው የማዕበል ፈጠን መጽሐፍ በቅኔ ክንዱ ታቅፎ አወረደልን።
ግሥት ሳባ ሰሎሞንን የፈተነችበት የጥበብ እንቆቅልሽ ይህ
መስለኛል፤ ከዚህ በኋላ ጠቢቡ ሰሎሞን ዝናዋን ሰምቶ ወደ ኢትዮጵያ
መጣ እንጂ ኢትዮጵያ ወደ እርሱ አትሄድም፤ ከሰሎሞን የሚበልጠው
ነውና!ይህ መጽሐፍ በዘመናዊ ትምህርት ብቻ ተሳፍሮ ከኢትዮጵያ
ሰፍና የወጣውን ትውልድ ወደ ኢትዮጵያዊ እሳቤ የሚመልስ
ክንፍ መርከብ ነው። ከተዋነይ የሕይወት መንገድ መቀላቀል ለሚሹ
ይወት መንገደኞች የተዘረጋ የጥበብ ድልድይ እነሆ!!

ሊቀ ሊቃውንት ስምዐ ኮነ መልአክ

# መግቢያ

አምናና ታች አምና ለዐሥሩ ጣቶቼ ሥራ አልነበራቸውም። ለአ... ጣቶቼ ሥራ ፍለጋ ደጋ ስወጣ፣ ቆላ ስወርድ ከዓመታት በፊት ነበልባ... የሚባል የቅኔ ዘራፊ

"በቅኔያችን ጥበብ በያዝነው ሆሣዕና፣

እንነጠቃለን በግዙፍ ደመና"

ከሚለው ቅኔ "ጥበብ ተቀብራለች" ብሎ የነገረኝ ትዝ አለኝ። ቅኔዉን ከልጅነቴ ጀምሮ እኔም አውቀዋለሁ። የሊቁ ክፍለ-ዮሐንስ መወድስ ነው። ሊቁ ክፍለ-ዮሐንስ በዘመኑ ባንዲት ዕለት፣ በተመሳሳይ ሰዓት በጎንደር ደብረ ብርሃን ሥላሴና በሸዋ ደብረ ብርሃን ሥላሴ ቅኔ-ማኅሌት ሲያገለግል ይውል ነበር። በዚህ ጊዜ የሸዋ ሊቃውንት ሊቁ ክፍለ-ዮሐንስ ከእነሱ ጋር በመንፈሳዊ አገልግሎት እንደ ዋለ በኩራት ሲናገሩ የጎንደር ሊቃውንት ደግሞ በጎንደር ደብረ ብርሃን ሥላሴ እንደ ልማዱ አዳፋ ልብሱን ለብሶ ቅኔውን ሲገጬው መዋሉን ይናገራሉ። ባለ ቅኔዉ በተመሳሳይ ሰዓት ጎንደርና ደብረ ብርሃን ሥላሴ በመንፈሳዊ አገልግሎት ስለማሳለፉ ሲጠየቅ፡-

"ንሕነሂ በግብረ ቅኔ ዘበሆሣዕና፣

እምአደ ገፋዒ ወተገፋዒ ንትመሰጥ በደመና" ሲል በመወድሱ መለሰ፡፡ ቅኔው ከላይ ከላይ ሲተረጎም፣

‹ብቅኔያችን ጥበብ በያዝነው ሆሣዕና፣

እንነጠቃለን በግዙፍ ደመና" እንደ ማለት ነው፡፡ ነበልባል እንደ ነገረኝ በዚህ ቅኔ ውስጥ ጥበብ ተቀብራለች"

ነበልባል ሌላም ተመሳሳይ ታሪክ ሲናገር እንዲህ ብሎ ነበር፡፡

"ከኢትዮጵያውያን ጠቢባን ሌላው ደግሞ ተዋነይ ይባል ነበር፡፡ ጠቢቡ ተዋነይ ከጎጃም ቅኔ ተቀኝቶ በተመሳሳይ ሰዓት ጎንደር ይደግም እንደ ነበር ዜና-ጥበቡ ይጠቁማል፡፡ ይህንን የኢትዮጵያ ዕፁብ ድንቅ ጥበብ የቅኔ ሊቃውንት በኩራት ይናገሩታል፡፡

ባላገሮችም

‹‹ተዋነይ በጣና

ይመስላል ደመና" ሲሉ ተዋነይ በደመና መጋለቡን ይተርካሉ" ብሎኛል ነበልባል፡፡

ነበልባል የነገረኝን ምሥጢር ለዐሥሩ ጣቶቼ ነገርኳቸው፡፡ ሥራ እን ፈጠርሁላቸው ቆጠሩት፡፡ ከዘመናት በፊት የነበረውን ሀገራዊ ፍልስፍ እየተሻሙ መከተብ ጀመሩ፡፡ ባለ ቅኔው ክፍለ ዮሐንስ መጣ፡፡ ተዋነ ተገለጠ፡፡ ሌሎችም ሊቃውንት በየተራ መጡ፡፡ አሥሩ ጣቶቼ በቅኔ ውስጥ የተቀበረውን ምሥጢር ሀገርኛ ብዕር፣ጨብጠው መከተ

ሲጀምሩ ጠቢቡ ሖረ ኩራዝ ለኮሱ። ወዲያው ግን ነፋስ
ገብቶ አጠፋባቸው። ሊቅ ዐፅቁ ሐሽማል የሚባል በጨለማ ውስጥ
ብርሃን የሚፈነጥቅ መጽሐፍ ይዘው ብቅ አሉ። ሐሽማል
ጨለማ ገፈፈው። ዐሥሩ ጣቶቼ ሲከትቡ እኔን እንቅልፍ
ጠቢቡ ሖረ ተሰውረዋል። ሊቅ ዐፅቁም ሐሽማልን ይዘው
ወጥተዋል። ዐሥሩ ጣቶቼ አንድ መጽሐፍ ጽፈዉ ስለ
ሲጨቃጨቁ ደረስሁ። ስሙን ሐሽማል በሉት አልኋቸው።
ብለው ጠሩት። እነሆ ሐሽማል ሆነ!!

ማዕበል ፈ

## ፩

ከዘመናት በፊት ውቢቱ ኢትዮጵያ በሊቃውንት ተጥለቀለቀች፡፡ ታላቋ ከተማ ጎንደርም በሊቃውንት ቅኔ ክብሯ ተወሳ፡፡ የሊቃውንቱ እግር ወደዚያው ፈጠነ፡፡ ሰማዕቱ ኖላዊ በጎንደር ከተማ ለማስተማር ደፋ ቀናማለት በዛባቸው፡፡ እግረ መንገዳቸውንም ከጎንደር ምሥጢራዊት ውኃ እየቀዱ ወደ ፊት ትልቅ ሰው ሆኖ ሀገር ይጠቅማል፣ ወገን ይረዳል ላሉት ያድሉ ያዙ፡፡ ምሥጢሩ ከእሳቸው አልፎ ከባዕድ ጆሮ እንዳይደርስ እየተጠነቀቁ ሲያድሉ ዓመታት አለፉ፡፡ ቀስ በቀስ የጎንደር ልዕልና በጠቢባን ልሳን ተወራ፡፡ ክብሯ የጸሐፍት ድርሳናትን አጨናነቀ፡፡ ምሥጢራዊው ሊቅ ኖላዊም እንደ ቅድመ አያቶቻቸው እንደ-ክፍለ ዮሐንስ በደመና እየተንቀሳቀሱ ጭምር ስለጎንደር ልዕልና፣ ስለ ኢትዮጵያ ረቂቅ ፍልስፍና ባራቱ ማዕዘን ላሉ ሀገርኛ ሊቃውንት ሹክ አሉ፡፡ ጭምጭምታው ከምዕራባውያን ብልጥ ጆሮ ደረሰ፡፡ ምዕራባውያን ቄስ መስለው መስቀል ጨብጠው ኢትዮጵያን ከመውረር በማይተናነስ መልኩ ሰፈሩባት፡፡ በተኮላተፈ ቋንቋቸው፣ በአዳዳ ምላሳቸው የውሸት ስብከት መስበክ ጀመሩ፡፡ ዳር ዳሩን እየሰበኩ መኻል ጎንደር ሲደርሱ የጎንደር ሊቃውንት 'የቀበሮ ባሕታዊ ከበግ መኻል ይሰግዳል' ሲሉ ዘበቱባቸው፡፡ ተልእኳቸው እንደ ከሸፈ ሲረዱ የስብከታቸውን መርሕ አስተካከሉ፡፡ በተለይ ጀርመን ከኢትዮጵያ የግእዝ ሊቃውንትን አጥብቃ እንደ ምትፈልግ ለንጉሡ አስረዱ፡፡ ንጉሠ-ነገሥቱ ባራቱ ማዕዘን ያሉ ሊቃውንት እንዲጠሩ አዋጅ ነገሩ፡፡ የደከመ በምርኩዝ፣ የታመመ በደጋፊ

እየታገዘ በሳምንት ቤተ-መንግሥቱ ቅኔ ቤት ሆነ። ከጎንደርም ሊቁ ኖላዊን ጨምሮ ዐራት ሊቃውንት ተጠርተው ነበር። ሦስቱ ወደ ጎንደር ሲመለሱ ንጉሡ ታዋቂውን ሊቅ ኖላዊን ወደ ጀርመን ልከው ጀርመንን በግእዝ እንዲያበለጽጉ አዘዙ። ተልእኮው እውን ሆነ። ሊቁ ጀርመን ሲገቡ ጀርመናውያን አደባባይ ወጥተው የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ እያውለበለቡ ተቀበሏቸው። የሊቁ ፎቶ-ግራፍ በጀርመን ከተሞች ከዚያም ከዚያም ተሰቀለ። በተንጣለለው የጀርመን ቤተ-መንግሥት የእራት ግብዣ ላይ ተገኝተው መወድስ-ቅኔ አሰሙ።

ሊቁ ከሳምንት በኋላ ግእዝ ቋንቋ በማስተማር ተጠመዱ። የጀርመን ምሁራን ከጥቁሩ የሐበሻ ሊቅ እግር ሥር ተኮለኮሉ። ሐበሻን እንደ ጥቁር ውሻ የሚቆጥሩ ነጮች ለዓላማቸው ሲሉ ቍንጽል ቀበሮ መሰሉ። ሊቁም ቀያይ ቀበሮዎችን ግእዝ ቋንቋ ማስቆጠር ጀመሩ። ቀያይ ቀበሮዎች ግን ከግእዙ ትምህርት ይልቅ ስለ ኢትዮጵያ የጥንት ጥበብ ሲጠይቁ ሀገራዊ ምሥጢር ላለመግለፅ ሊቁ ሲሸሹ ኖሩ።

ከዓመታት በኋላ ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ሲዘጋጁ በድንገት ሕይወታቸው አለፈ። ሕልፈተ-ሕይወታቸው እንደተሰማ እነ አባ ደመና ጎንደርን እየዞሩ ለፈፉ። አስከሬናቸው ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ለብሶ፣ ጎንደር ሲገባ ጠቢባን በተለያየ የሥራ ዘርፍ ተጠመዱ። ቀብራቸው አጨቃጫቂ ሆነ። መላ ጎንደር ተሰበሰበ። የጀግኖች ማኅበር በጀግኖች ወግ እንዲቀበሩ ወሰነ። ሊቃውንቱ በሊቃውንት ወግ መሆን አለበት ሲሉ ውሳኔውን ሻሩ። ጠቢባኑ በጠቢባን ወግ እንዲሆን ዲኮ ታጥቀው ተከራከሩ። ይህንን ተከትሎ በጎንደር ከተማ ጭቅጭቅ ተፈጠረ። ነገሩን

የሚፈቱ አንጋፋ ሊቃውንት ተመረጡ:: ከሊቃውንት ክፍል ሊቀ ዐፅቁ ተወከሉ:: ከጀግኖች ማኅበር በኩል ደግሞ ዐራትጀግኖች ተመረጡ:: ከጠቢባኑ ድንቁ ዘጎንጅ ተገኙ:: ጉባኤው በገነት ተራራ እንዲሆን ወሰኑ:: በገነት ተራራ ላይ ተደረገ::

ጠቢባኑ ወደ ገነት ተራራ ሊያመሩ ብልኮ ሰፈር ሲደርሱ ሁሉም ነገር በዝምታ ተሸብቧል:: የብልኮ ባሕላዊ ቤቶች በዝምታ ተለጉመዋል:: የብልኮ አታሞ ወዲያ ተከላትማ ወድቃለች:: የምሽት ቤቶችን በመሰንቆ የሚያጠምቁ አዝማሪዎች ብልኮን እስከ ወዲያኛው የረሷት ይመስላሉ:: ብልኮ እንደ ጣና ገዳማት በጸጥታ ተውጣለች:: የመሰንቆም ሆነ የአታሞ ድምፅ አይሰማባትም:: ባሕላዊ ቤቶች የባሕሉን እያደረሱ አይደለም:: በባሕል ምሽት አንድ ብርሌ ጠጅ በስሙኒ እንዳልሸጡ ከንግድ ዓለም መንነዋል:: ፀሐይ ወደ መስኮቷ ስታቄለቍል ጠቢባኑ በአንድ አሮጌ ጋሪ ታዝለው ከዐጤ ቴዎድሮስ አደባባይ ወደ ገነት ተራራ አዘገሙ:: ባለጋሪው የሊቃውንቱን ሻሽ ሲመለከት ሙዚቃውን ዘግቶ መዝሙር ከፈተ:: ጠቢባኑ ግን ለመዝሙሩም ሆነ ለሙዚቃው ጆሮ የሰጡት አይመስሉም:: በዚያውም ላይ የጋሪው ጎማዎች በጠጠሮች መንፈራገጥ ሲጀምሩ የመዝሙሩ ለዛ ጠፋ:: ዘማሪው ጥሩ ድምፃዊ ቢሆንም የዜማው ጣዕም ከጋሪ ኳኳታ ጋር ሲደመር ቃናው ከሰመ:: ባለጋሪው ለሙዚቃውም ሆነ ለመዝሙሩ ትኩረት እንዳልሰጡት ሲመለከት ድምፁን አጥፍቶ እየተጠማዘዘ ቀጥታ ወደ ገነት ተራራ አመራ:: ጋሪው በሲቃ ገነት ተራራን አቋርጦ ወደ ቁንጮው ሊደርስ ጥቂት ሲቀረው እንዲያቆም ምልክት ሰጡት::

ባለጋሪው ዳኘቱን ሳይፈጽም እንደ ምንም ብሎ ፈረሱን እስከ ጋሪ
ገታ። አሣውንቶች ቀስ ብለው ከወረዱ በኋላ ለባለ ጋሪው ከኪሳቸው
እየመገርለጡ ስሙኒ ስሙኒ ሳንቲም ሸጎጡለት። ባለጋሪው አሮጌ ፈረሱን
ወደ ኋላ መልሶ ሲፈተለክ ታሪክ ነጋሪዎቹ ገነት ተራራ ላይ ወጥተው

ጉብ አሉ። ሰዓቱ ተጎድቶ ምድር መሽቶ ነበር።

ጉባኤው እንደተጀመረ ከጀግኖች ማኅበር ወገን በቀብራቸው ቀን ትልቁ
ስውሊቅ ዐፅቁ መድፍ መተኮስ እንዳለባቸውና ቀብሩም በጀግኖች ማኅበር
ወግ እንዲሆን የጀግኖች ማኅበር ሲወስን ሊቀ ዐፅቁ ሐሳቡን በሐሳብ
ለመሻር መቋሚያቸውን ተደግፈው ተነሡ። ሲነሡ ወገባቸው
ቀ…ሽ…ቀ…ሽ ሲል ተሰማ። በጥሬ የደቀቀ የካህን ወገብ ይህንን መሰል
ድምፅ ማሰማቱ የተለመደ ስለሆነ ብዙ አትኩሮት የሰጠው አልነበረም።
መምሬ ገጻቸውን በመስቀል አማትበው፣ ዐራቱን ማዕዘን ባርከው፣ በሰባቱ
ሰማያት አምሳል የተፈጠሩ ሰባቱን የጎንደር ተራሮች ቃኝተው መናገር
ጀመሩ።

"በቅድሚያ ለማዕቱ ኖላዊን አስመልክቶ ስለተናገራችሁት ጠቃሚ ሐሳብ
ከልብ ከልብ አመሰግናለሁ። የተናገራችሁትን ሁሉ ገቢራዊ ለማድረግ
ግን የሃይማኖቱ ሥርዐት አይፈቅድም። ቢፈቅድልኝ ኑሮ መድፉን
መተኮስ ቀላል ነበር። ግን እንኳን መተኮስ ባርኮ መስጠት ክልክል ነው።
እኛ ኢትዮጵያውያን የድሮ ፋሽስት ጻጻሳት አይደለንም። ቀኖናችንም
አይፈቅድልንም…።" ብለው ትንሽ ስለ ክብረ ክህነት ተናገሩ።
የክብረ ክህነቱን ምሥጢር ዘርዝረው አስረድተው እንዳበቁ፤

“ቀኖናው በሚፈቅደው መሠረት እንጂ በዘፈቀደ ደግሞ የሚሆን ነገር የለም። ሊቀ ኖላዊ አርበኛ መሆናቸውን ወዳጃቸው ቀርቶ ጠላታቸው ይመሰክራል። በጠላት ወረራ ጊዜ ከታቦቱ ጎን ሆነው፤
‘እሳቱ የሀገሬ ጀግና፣
እየፎከረ ይገላል ገና’ እያሉ አጽንዖት ሲሰጡ አርፍደው ወደ መጨረሻ አካባቢ ከአባት አርበኞች እኩል ተሰልፈው ተዋግተዋል። ድል መተዋል። ያን ጊዜ እኔም እንደ ዐቅሜ በዲቁና እያገለገልሁ ቃጭል እያቃጨልሁ አብሬ ነበርሁ። ተዋግተዋል። ማርከዋል። በከባዱ ቆስለዋል። እግራቸው ግድም እንደተመቱ ትዝ ይለኛል። ተመተው ግን አላፈገፈጉም። ከጠላት ለተወረወረ አጻፋ መልሰው ያንን የመታቸውን ወታደር እስከ መሣሪያው ማርከው በምሕረት እንዳለፉት ትዝ ይለኛል። እንደ ጌታችን ማርኮ መማር ያስተማሩ መምር እየተባሉ ሲመሰገኑ ሰምቻለሁ። ይህን አውቃለሁ። ቁስላቸውን በዐይኔ በብረቱ ተመልክቻለሁ።” ብለው እንባ ቀድማቸው። በመሐረባቸው ጫፍ ዐይናቸውን ጠርገው ተረጋግተው እንደ ገና መናገር ጀመሩ።

“እኔን ያሳሰበኝ የመድፉ ሳይሆን የጸሎቱ ጉዳይ ነው። ነፍስ ከሥጋ ስትለይ ጀምሮ የሚጸለይ መጽሐፍ አለ። መዋቲው ከሞተበት ቅጽበት ጀምሮ የሚጸለይ መጽሐፈ-ሙታን ነው። መጽሐፉ ከብሉይ ኪዳንና ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተውጣጣ ሲሆን ለሙታን ብቻ የሚጸለይ የተለመደው ነው። ጸሎቱ ለሙታን የሚጸለይ ሲሆን፣ የተለያዩ የማዕረግ ክፍሎች አሉት። የምሁርና የመነኩሴ፣ የሴትና የወንድ በሚል አንቀጽ ተከፋፍሏል። ይህ የወረቀቱ መጽሐፍ የሚያዝዘው ክፍል ሲሆን

የብራናው ግን የሊቃውንት፣ የፈላስፎችና የጠቢባን ክፍሎች፣ ይጨምራል:: በእውነት ሊቁ በአርበኞች ወግ ይቀበሩ ቢባል ይህ ሁሉ ቀኖና ይፋለሳል:: መቼም 'ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ' እንደሚባለው ሁሉ ለሰማዕቱ ያልሆነ ብራና ባዶ ቁርበት እንጂ በምሥጢራዊ ቀለም የታጨቀ ምሥጢራዊ ብራና ሊሆን አይችልም:: ስለዚህ በቀብሩ ጊዜ ለንባብ የሚቀርበው የብራናው መጽሐፍ ነው:: መቼም ለሊቁና ለሰማዕቱ ክብር እንኳን በብራና ሌጦ፣ በድንጋይ ሰሌዳ፣ የተጻፈ ቀለም እንደማይገልጣቸው እሙን ነው:: መጻሕፍት ሁሉ ተሰብስበው ቢነበቡ ያንሱባቸዋል እንጂ አይበዙባቸውም:: የሊቁንና የሰማዕቱን ክብር በትክክል ይገልጣሉ ብዬ አፌን ሞልቼም አልናገርም:: ተነብበው ቀርቶ አፍ አውጥተው ቢመሰክሩ እንኳን ክብራቸውን አይገልጡም:: የሆነው ሆኖ በአባታቸው በዐጤ ፋሲል ዘመን ተጽፎ፣ በአድያም ሰገድ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት የተተረጎመው የግእዙ ብራና መቅረቡ አይቀርም:: ያንን ብራና እንዲያመጣ የመጻሕፍት ክፍል ኀላፊዉን አዝዣለሁ:: ብራናው ሲወጣ ከብዙ ሞጭላፊዎች ዐይን ውስጥ እንደሚገባ አላጣሁትም:: ቢሆንም 'ሕልም ተፈርቶ' እንደሚባለው ሌባ ተፈርቶ ሊቀ-ሊቃውንቱን በወረቀት በተጻፈ መጽሐፍ ጸልየን አንሸኛቸውም:: ጥቅልሉ ብራና መቅረብ አለበት::" አሉ::

"ይህ መጽሐፍ ከሌሎች መጻሕፍት በምን ይለያል?" አለ አንድ ሰው ከመኻል ጣልቃ ገብቶ::

"መጽሐፉ ሐሸማል ይባላል:: ትርጉሙን እንዳትጠይቁኝ:: ይህ መጽሐፍ ከተለመደው ላይ ሁለት ነገር ይጨምራል::"

"ምን ምን?" አለ ጠያቂው ሰውዬ።

"ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በወረቀት የታተመው መጽሐፍ የጠቢባኑንና የሊቃውንቱን ክፍል አያካትትም። በሀገራችን ሊቃውንት በምሥጢራዊ ቀለም የተጻፈው የጥንቱ ብራናው መጽሐፍ ግን የጠቢባኑንና የሊቃውንቱን ክፍል ይጨምራል።" አሉ ሊቅ ዐፅቁ ሲመልሱ።

"ቃሉስ ይለውጣል? ወይስ በወረቀትና በብራና ላይ መጣፉ ነው ልዩነቱ?" አሉ ያው ቄስ ቀመስ አረጋዊ ማብራሪያው በደንብ ስላልተረዳቸው።

"ቀለሙም ልዩ ነው።" አሉ ሊቅ ዐፅቁ።

"ቀለሙም ልዩ ነው። ልዩ ነው ማለቴም የኀብረ ቀለማቱን ዝርዝር ቀይ ጥቁር ነጭና ቢጫ መልክ ይገልጣል ለማለት አይደለም። አባቶቻችን ለመጽሐፉ የተጠቀሙት ኅብረ-ቀለም ውስጠ ወይራ ነው ማለቴ ነው።" አሉ ሊቅ ዐፅቁ ኮስተር ብለው።

"...ለምሳሌ ጠቢባን ሲያርፉ 'ልብየ ርእየት ብዙኀ ጥበበ' የሚለው ክፍል ይነበባል። ትርጉሙም 'ልቤ ብዙ ጥበብ ናፈቀች' ማለት ነው። ሊቃውንት ሲሞቱ ደግሞ 'ተንጥአ ሊቅስ እኩይ ውእቱ' የሚለው ሽካራው ክፍል ጎላ ባለ ድምፅ በጥሩ አንባቢ ይነበባል። ትርጉሙና ንባቡ ፈታኝ ነው። ውሽክሽክ ቄስ ሊያነበው አይችልም። ከታወቁ ሊቃውንት በቀር ውሽክሽክ ቄስ ሲይዘው መጽሐፉም ዝም ቄሱም ዝም ናቸው። አይጣጣሙም። መጽሐፉ በእውቀት የበሰለ ብራና ላይ የሰፈሩ ቀለማትን በወረቀት ከሠፈሩ ቀለማት ለይቶ የሚያነብ የንስር ዐይን ያለው ሊቅ ይጠይቃል። ዛሬ ዛሬ ብራናውን መጽሐፍ ቀርቶ ወረቀቱን አቃንቶ

አያደርስም:: አንተ ቅኔ እያስተማርህ ይቺን ምሥጢራዊት ውኃ ለመጭው ትውልድ ማድረስ አያቅትህም:: ለአብነት ተማሪዎች ቅኔ እያስተማርህ ቀለም እየነገርህ ትጠብቃታለህ::" ጠቢቡ ሐረ ወደ ታብር እየተመለከቱ ነገሩን ቀለል አድርገው ገለጹት::

"አንተስ?"

"እኔም እንደ ዐቅሜ "ስማዕቱ ኖላዊ" የሞተላትን ምንጭ እፈልጋለሁ:: በተለይ ይቺን ውኃ ከስማዕቱ ኖላዊ እጅ ማን እንደተረከባት ባውቅ ፍለጋው ይቀልልኝ ነበር:: ግድ የለም:: እድሜ ዘመኔን እንደ ተጠማ ዋልያ ውኃ ስፈልግ እኖራለሁ::" ብለው ከልሙጡ ድንጋይ ላይ ተነሡ::

ከዚያም "በል አሁን እኔን በሰላም ሸኘኝ?" አሉ ጠቢቡ ሐረ ጥቂት ራመድ ራመድ እያሉ::

"ክእንዲህ ወዲህ ያችንን ውኃ ሳታገኝ ፊቱን አታየውም::" አሉ ወጣቱ ፋሬስ ሐረን እየሸኙ::

"እሱን ለኔ ተወው:: ዋናው ነገር አንተ እንደ ዐጤ ቴዎድሮስ ጀግና ሁን:: በታብር በኩል ከመጣ የሞት ጽዋ ከኔ ይለፍ ማለት የለብህም:: ቀስ ብዬ ስለልህ አልፎ አልፎ ወላዋዩ ቢጤ ነገር ነህ:: ውስጠ መሠረትህን ብዙ ሰዎች ስለማይረዱ በቀላል ነገር ሊደልሉህ ሊመጡ ይችላሉ:: ጥንቃቄ አድርግ:: በተለይ ተራዳኢ መልአክ መስሎ ከሚመጣ ሰይጣን ተጠንቀቅ::" ብለው ሐረ መንገድ ሲጀምሩ ፋሬስም ቆልማማ ከዘራቸውን እየተመረኮዙ ተከተሉ:: ከትልቁ ከተዋነይ ዋርካ ጀምረው ወደ ሰሜንመስዕ ጥቂት ተጉዘው ታብር በር ላይ ሲደርሱ "ስማቸውንና የመጽሐፉን ስም እንዳትረሳ አደራ:: የመጽሐፉ ስም ሐሸማል ነው::






ይህንን መጽሐፍ ይዘው በጎንደር ውስጥ የሚኖሩት ምሥጢር አዋቂዉ ሊቅ ደግሞ ሊቅ ዐዕቱ ይባላሉ::" አሉ ሊቁ ፋሬስ ከዓመታት በፊት ድንቁ ቃል በቃል የነገሯቸው ስም ትዝ ብሏቸው::

"ጎንደር ስትደርስ ስማቸውን ጠይቅ:: የሚያውቅ ከሌላ በዐበቅ የለሽ ግደም ፈልጋቸው:: የድሮ ሰው ስለሆነ ከጠጇም ከመሸታዋም የወጉን ሳያደርሱ አይውሉም ሲባል ሰምቻለሁ መልካም መንገድ!! ሰፈራቸው እጨጌ ሰፈር ነው::" ብለው ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ጠቢቡ ሐረ ወደ ፊት ገሠገሡ:: ሊቁ ፋሬስ እየቆዘሙ ወደ ተዋነይ ዋርካ ሲመለሱ የቅኔ ተማሪዎች ቅኔ ቆጥረው እየተመለሱ ነበር::

# ፫

## ጎንደር

ጠቢቡ ሐረ ከፋሬስ ተለይተው ወደ ጎንደር ደርሰው በጨለማ ውስጥ ፊደላቱ ቀያይ ብርሃን የሚፈነጥቁ ሐሸማል የሚባለውን የጥበብ መጽሐፍ የያዙትን ሊቅ ዕፅቁን አግኝተው የሕይወትን ውኃ ለመቅመስ እንደ ቋመጡ ገጻቸው ያስታውቃል:: ጎንጅ ደብረ-ጥበብ ተነሥተው ጎንደር እስኪደርሱ ድረስ ይህንን ሐሳብ ሲያወጡ ሲያወርዱ መንገዱ ብዙ ቀን አልፈጀባቸውም ነበር:: በተለይ ሊቁ ፋሬስ "ያችን ውኃ ሳትይዝ ፊቴን አታየውም:: የመምህሩንና የመጽሐፉን ስም እንዳትረሳ" ያሉትን እያስታወሱ ሰነበቱ::

…ይህን ቃል እንደ ውዳሴ-ማርያም እየከለሱ፣ እየመለሱ፣ ከጎጃም ተነሥተው በአዲስ ዘመን በኩል አቋርጠው በሦስተኛው ቀን ጎንደር ገቡ:: ጎንደር እንደ ደረሱ በደረታቸው ተንበልብለው የጎንደርን መሬት ሳሙ:: ዐፈሩን ቃሙ:: ከዚያም በውኃ ጥም የደረቀ ጉሮሯቸውን አርጥበው እግራቸውን አጥፈው እግረ-መንገዳቸውን የሊቅ ዕፅቁን ሰፈር ለመጠየቅ ከአንዲት በረንዳ ላይ ቁጭ ብለው ቡና ወደሚጠጡ ሰዎች ጐራ አሉ:: ለራሳቸው በአኮፋዳቸው ከያዙት ጥሬ ሽንብራ እየቆረጠሙ የእግዜርን ውኃ እየተጐነጩ ቀሪ ጉዳያቸውን ማሰላሰል ጀመሩ:: በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ቀይ ብርሃን የሚያበራውንና ባሕር የሚያነድደውን የጥበብ መጽሐፍ እጅ ካደረጉ በኋላ በመጽሐፉ መሪነት ቀጣዩ ጉዞ ፍንትው ብሎ በአእምሯቸው መጣ:: የምኞት ፊታቸው ፈካ::



"እላጣውም!" አሉ ሰው እስኪሰማ ጮኽ ብለው:: ድካም ይጠይቃል እንጂ መጽሐፉ…" በረንዳ ላይ ክብ ሠርቶ ቡን የሚጠጣው ሰው ቀና ቀና እያለ ሲመለከታቸው ድንጋጤ ወረራቸው:: ወደ ጥሬዋ አቀረቀሩና በመዳፋቸው ቸርፍሰው ቃም ቃም አደረጉ:: ድፍርሱን ውኃ ጅ..ው..ው..አደረጉ:: በአትኩሮት ቀና እያለ የተመለከታቸው ሰው ወደ ቡናው አቀረቀረ:: መቀመጥ የሰለቸው ሒሳብ እየከፈለ ውልቅ አለ:: ጠቢቡ ሐረ እንደገና በውስጣቸው ማሰላሰል ያዙ::

"የመጀመሪያው ሥራዬ ሊቅ ዐፅቁን ፈልጎ ማግኘት:: ቀስ በቀስ መጽሐፉን በጥብቅ መመርመር:: ከዚያም በመጽሐፉ ምሥጢራዊ ቀይ ብርሃን እየተመራሁ የሕይወትን ውኃ ማሠሥ:: ያንን ሳገኝ ወደ ሁለተኛው ሥራዬ እገባለሁ…::" ይበልጥ ይኸኛው አእምሯቸውን ሰቅዞ ያዘው:: ወደ ጥበብ ዓለም በፍቅር ተስበው የገቡበትን ቀን መረቁ:: ቀና ብለው በጎንደር ሰማይ ላይ የሚውረገረገውን ደመና ተመለከቱ:: በደመና ተጭነው በኢትዮጵያ ሰማይ ሲንሳፈፉ በዐይነ-ሕሊናቸው ው..ል አለባቸው:: ይህንና ወደ ፊት ከሞት ተሰውረው የሚኖሩትን ምሥጢር ሲያስቡ ነፍሳቸው በፍሥሐ ያለ ጊዜዋ ቱ..ር..ር.. ብላ ልትወጣ ነበር:: ምኞት እንደ ሰብ ተናንቋቸው መተንፈስ አቅቷቸው ገጻቸውን ሲያኮሳትሩ ጥሬዋ ሽንብራ ጉሮሯቸው ላይ ቁማ ላብ በላብ አደረገቻቸው::

ከዚያም ስመ-እግዚአብሔር ጠርተው ዐማትበው ከሐሳባቸው እንደ ምንም ባንነው ወደ ራሳቸው ሲመለሱ ፈገግ አሉ:: ከፊት ለፊት ቡን

ዓመት መልአከ ሞትን የገዘተ ሊቅ ነበር" እያሉ የነበረውን እንዳልነበረ አድርገው ሲከትቡ ይታያሉ፡፡ እሱን ገልጠን ማስተማሩ የእኛ የሊቃውንቱ ድርሻ ነው፡፡" አሉ ሊቁ ፋሬስ፡፡

"የትኔውን ሰምና ወርቅ ግን አማናዊ አድርገን መውሰድ እንችላለን?" አለ ነበልባል፡፡

"እንወስደዋለን!፡፡" ፋሬስ ራሳቸውን ባንቱታ አንቀለጸጸሉ፡፡

ሊቁ ፋሬስ የእድሜያአቸውን ግማሽ የጨረሱት በቅኔ ትምህርት ነው። ደብረ-ቢዘን፣አክሱም ጽዮን፣ ቤተ-ቀጢን፣ ዋድላ ደላንታ፣ ጎንደር ገለዓድ ቅኔ ቤት፣ደብረ ምእራፍ ዋሸራ ማርያም፣ ዲማ ጊዮርጊስ፣ በሸዋም ደብረ ብርሃን ሥላሴ፣እንኮበር ሥሬ መድኃኔ ዓለም፣ አዲስ ዓለም ገዳም ሌሎችም ዛሬ በከፊል የጠፉ የቅኔ ትምህርት ቤቶች የሊቁ የፋሬስ የቀለም ሀገራት ነበሩ፡፡ ከእኒህ ቅኔ ቤቶች ሲማሩ አድገው በመጨረሻ በጎጃም ክፍለ-ሀገር ጎንጅ ደብረ-ጥበብ ከተዋነይ ቅኔ ቤት ትምህርታቸውን አሣረጉ፡፡ የጎንጁ ሊቅ ድንቁም ከቀለሙ ጎን ለጎን የታብርን ምሥጢር መረቋቸው፡፡ ሊቁ ፋሬስ የምሥጢር ሰው ሆኑ፡፡

ነበልባልም ቢሆን ቀላል ተማሪ አይደለም፡፡ በዐራቱ ማእዘን ዘር ቀለም በማጥናት ደክሟል፡፡ 'የሺ ፍልጥ ማሠሪያ ልጥ' ነውና እስካሁን የሰበሰበውን የሚያሥርበት ሐረግ ለመሳብ ጎንጅ ደብረ-ጥበብን ተቀላቀለ፡፡ ልቦናው ከታብር ለመቋደስ ፈለገ፡፡ ጎንጅ ሲደርስ ግን በቀለም አያያዛቸው ፋ-ና-ወጊው ሊቅ ድንቁ አልፈው ፋሬስ በቅኔ ዙፋናቸው ተተክተው አገኘ፡፡



ድንቁን በአካል ቢያጣቸውም ቀለማቸው በፋሬስ ልብ ተጽፎ፣ መወድሱ ደምቆ ተቀበለው፡፡ "መጠኑ ለረድዕ ከመ ሊቁ" የደቀመዝሙር መጠኑ እንደ መምህሩ ቢሆን ነው የሚባለው ቃለ-ወንጌል በፋሬስና በሖረ የልብ ጽላት ተጽፎ ነበር፡፡

ክርክሩ ቀጠለ፡፡

"የኔታ ቅኔው በደንብ አልገባኝም፡፡ በደንብ መረዳት እፈልጋለሁ?"

"ምኑ ነው ያልገባህ?" አሉ ሊቁ ፋሬስ፡፡

"ሰምና ወርቁ?"

"ቅኔው በሰምና በወርቅ ላይ ብቻ የተቀነበበ አይደለም፡፡ ቅኔው የሚገልጠው ሌላ አዲስ ምሥጢርም አለው፡፡ ያንን ደግሞ እየቆየህ ትደርስበታለህ፡፡" አሉ ፋሬስ፡፡

"ዛሬ ቃል በቃል ጠይቄ ካልገባኝ ሌላ ጊዜ እንዴት ልደርስበት እችላለሁ?" ነበልባል ወደፊት የሚደርስበት ቅኔ ብቻ መስሎት በጥያቄ ትንፋሽ ነሣቸው፡፡

ሊቁ ማብራራት ቀጠሉ፡፡

"የቅኔ መንገዶች በመቶ የሚቆጠሩ ሲሆኑ ጥቂቶቹን ብቻ ብናነሣ እንኳን እውታረ-ፊደል፣ሥራና፣ ዐይነ ውኃና ምርምር ቅኔ በመባል ይታወቃሉ፡፡ እኒህም የሃይማኖት የታሪክ የባሕል የፍልስፍና ምንጮች ናቸው፡፡ በተለይ ፍልስፍና-ነክ ቅኔዎች ለምርምር ይጠቅማሉ፡፡ ከሃይማኖት አስተምህሮው ወጣ ብለው በታሪክ በዕፅዋትና በጥበብ ላይ የሚያጠነጥኑ መወድሶች የጠቢባኑ የጥበብ ማኅተም ተቀርጾባቸው እናገኛለን፡፡" አሉ ሊቁ ፋሬስ፡፡

"ታዲያ ይህ ቅኔ ከማንኛው መንገድ ይመደባል? ዐይነ-ውኃ መንገድ ወይስ ምርምር ሰምና ወርቁ ምን ይባላል?" አለ ነበልባል::

"ቅኔው ምርምር ወይም ፍልስፍና አይደለም:: ከተለመደው የቅኔ መንገድ ወጣ ያለ ነው:: 'ዘጸንዐ ዴዴሃ ይበልዕ ፍሬሃ' እንዳሉ አበው ፍሬ-ነገሩ ወደፊት በዐይን የሚታይ ይሆናል::" ብለው ወደ ዕለቱ ጉባኤ ገቡ:: አንዱን ወጣኒ ተማሪ '-ና- ወዲህ ልጄ!' ብለው የቆጠረውን ቅኔ ሰምተው ለማስተካከል ጆሯቸውን ወደ ወጣኒው ተማሪ ዘንበል አድርገው ማዳመጥ ጀመሩ::

ነበልባል "እንዲያ ይበሉኝማ! እሰይ የኔ ባለ ቅኔ! ወደ ፊትማ እኔም ብዙ እጠብቃለሁ:: በቅኒቸው ደመና ሊሆን እንዴት ቻለ? ሮቢላቸው ጢስ? ደግሞ ጠቢባን? የጥበብ ሊቃውንቱ እነማን ይሆኑ?" እያለ በውስጡ ሲያወጣ ሲያወርድ ከናፍሮቹ እየተወራጩ ነበር::



# ፳

ጎንደር-እጨጌ ሰፈር ደረሱ::

ጠቢቡ ሖረ ሰዓቱ ለዐይን ያዝ ሲያደርግ ከእጨጌ ሰፈር ደረሱ:: አካባቢው ጭር ብሏል:: በእቅዳቸው መሠረት ስለ ሕይወት ውኃና ስለ ጎንደር ምሥጢር ያውቃሉ ብለው የቀለምና የጥበብ መምህራቸው አለቃ ድንቁ የነገሯቸውን ሊቅ ዕፅቁንና ሐሸማል የሚባለውን ባሕሩን እንደ ቤንዚን የሚያነድ መጽሐፍ ይኖርበታል ተብሎ ወደሚገመተው ሊቅ ዕፅቁ ቤት ለመሄድ ነበር::

ቀን ቀን ጠጅ በመሸጥ የሚታወቁት የእጨጌ ሰፈር ቤቶች ምሽቱን ተከትለው እንደ ወጉ ተዘጋግተዋል:: የጠጁ መዓዛ አልፎ አልፎ ያውዳል:: ጠቢቡ ሖረ ግራ ቀኙን የእጨጌ ሰፈር በከፊል እየገላመጡ ወደ እጨጌ ሰፈር ከደረሱ በኋላ በትትክል መጽሐፉና ሊቁ ይኖሩበታል ተብሎ የሚገመተው ከእጨጌ ቤቶች ውስጥ ደርብና ምድር ቤት ያለው ዋናው ቤት ግር አላቸው:: ቤቱን ለማረጋገጥ ለምልክት በሥዕለ አድኅኖ መልክ የያዙትን ከተጠረበ ድንጋይ ላይ የተሳለ ሥዕል ከአኮፋዳቸው አወጡ:: በጠቢባኑ አባቶች እጅ የተሣለው የቤቱ ምስል ደርብ አለው:: ከዚኛው ጋር በቅርፅም በደርብም አይገናኙም:: በዚህ መሠረት ደርብ በደርብ የተሠሩ ብሉየ-መዋዕል ቤቶችን እየመረጡ ይመለከቱ ጀመር:: በመጀመሪያ ከአንድ ብሉየ-መዋዕል ቤት ጋር ተጋጠሙ:: ቤቱ ደርብ ቢኖረውም የደርቡ መወጣጫ የተሠራው በእንጨት መሰላል ነው:: "አይደለም አይደለም! ይህ አይደለም!" ብለው አለፉት::

"አይዞዎት ጌታዬ አይዞዎት! አይደንግጡ! ወደ ማይቀርበት ዓለም መሄዳቸው ለእሳቸው ፍሥሐ ነው:: የቀሩብን ለእኛ ብቻ ነው:: ለዚች ደሃ ሀገር የረባ ውለታ ሳይውሉ መሄዳቸው እንጂ የሚያስቆረቁረው ለሲቁ ዕረፍት ነው:: ከጀርመን የተመለሰው በድናቸው ነው::" አለ ማንደፍሮ::

ከዚያም ወደውስጥ አስገብቶ እስኪረጋጉ ድረስ አረፍ እንዲሉ አደረጋቸው:: ጥቂት እንዳረፉ ውኃ አምጥቶ ፊታቸውን እንዲታጠቡ ካደረገ በኋላ ወግ ጀመሩ::

"ለመሆኑ መቼ አረፉ?" አሉ ጠቢቡ ሖረ::

"ስንትና ስንት ዘመን አለፋቸው"

"እርስዎ የቤቱ ወራሲ ነዎት?"

"አይደለሁም! ጥበቃ ነኝ::

"ሲያርፉ ቤቱን ማን ተረከበው ጌታዬ!::" አሉ ጠቢቡ ሖረ::

"ለጊዜው የተረከበው መንግሥት ነበር:: አሁን ግን ቤቱ ተሸጧል::" አለ ማንደፍሮ::

"ማ..ማን ሸጠው?" አሉ ጠቢቡ ሖረ::

"መንግሥት ተረክቦ ሳይውል ሳያድር በሃራጅ ሸጠው::" አለ ማንደፍሮ ጠብ-መንጃውን ወድሮ በጥልቀት እያጤናቸው::

"ማ...ማ..ን... ገዛዉ?" ጠቢቡ ሖረ አንደበታቸው እየተሳሰረ ጠየቁ::

"በቅርቡ ግእዝ ለማስተማር ጎንደር የገባ ጀርማናዊ ባዕለ-ጸጋ ነው አሉ::"





"...ጀ...ጀ..ጀ..ጀርመናዊ የፈጣሪ ያለህ! ጀርመናዊ በዚያውም ባለጸጋ! የፈጣሪ ያለህ!::" እያሉ በውስጣቸው ሲናደዱ ድጋሜ ላብ ዘፈቃቸው:: ማንደፍሮ ሁኔታቸውን ሲያጤን ቆይቶ ከሰውዬው ሞት የቤቱ መሸጥ ለምን ላብ በላብ እንዳደረጋቸው አልገለጥለት ሲል፤

"ይበሉ! ይነሡ ጌታዬ! ጊዜው እየመሸ ነው:: ወደ ማደሪያዎ ይሄዱ:: ዘንድሮ ይህ ቤት ጣጣ እያመጣ ነው:: ጣጣው እንደ ይተርፍዎ ቀስ ብለው ይውጡ::" አለ::

"የምን ጣጣ ልጄ?" አሉ ጠቢቡ ሖረ::

"ይህ ቤት ድሮ የእጨጌዎች ማረፊያ ብቻ ነበር ይባላል:: እጨጌዎች ሲያርፉ ቀስ በቀስ የጎንደር ፈላስፎች እየተፈራረቁ መጽሐፍ ሲያነቡበት ይኖሩ ነበርም ይባላል:: ፍሬ ፍሬ የሆኑ የጎንደር ሊቃውንትም ቤተ-ሙከራ አድርገው ተጠቅመውበታል:: ከባለ ቅኔው ክፍለ ዮሐንስ ጀምሮ ሊቃውንቱ በዚህ ስፍራ ተፈላስፈውበታል:: ከሊቃውንቱ አንዱ ሰማዕቱ ኖላዊ ይባሉ ነበር:: ሰማዕቱ ኖላዊ እጨጌ ሆነው በዚህ ስፍራ ሲኖሩ ወደ ጀርመን ሀገር ግእዝ ለማስተማር ሄዱ:: ቅዱስ የሆነውን የግእዝ ቋንቋ እያስተማሩ እስኪሞቱ ድረስ ይህንን ቤት ሲናፍቁ ነበር እያሉ ሲያወሩ እሰማለሁ:: እሳቸው ሲያርፉ ቤቱ "ቤተ መዘክር" ሆኖ በቅርስነት ይመዘገባል ሲባል መንግሥት ተረክቦ ጨረታ አወጣበት:: ይህንን የሰሙ የጎንደር ሊቃውንት እያጉረመረሙ ነው::" አለ ማንደፍሮ::

"የሊቃውንቱ ጉርምርታ ምኑ ላይ ነው?" ጠቢቡ ሖረ የማንደፍሮን እውቀት ለመሰለል ምንም የማያውቁ መስለው ተፈላሰፉበት::

